"ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" ሉቃስ ምዕራፍ ፩፥48

# <u>በእሷስ አትምጡብኝ</u>

በተንከባካቢዬ በፈጥኖ ደራሿ

ውሎ በማያድረው በድንቅ ምላሿ

በእሷስ አትምጡብኝ የለኝም መድረሻ

ያለችኝ እሷው ናት ለነፍሴ መካሻ።

በዘወትር ዝማሬዬ ድንግል እመቤቴ

በአለሁለህ ባዬ በሕይወት መሰረቴ

በእሷስ አትምጡብኝ በአንዷ ትምክህቴ

ከመስቀል ስር ግርጌ ባገኘሁአት እናቴ።

ሰላም ለኪ ሲሏት ሰሟ በሚጣፍጠው

በመዓዛ ሽታ ዙሪያውን በምታውደው

በእሷስ አትምጡብኝ ምልጃዋ ልዩ ነው

ለአልጫው ሕይወቴ ጣፋጭ መድኃኒት ነው።

በምስራቋ ደጃፍ በአስታራቂዩ

በጸሎቴ ምላሽ በዕንባ አባሽዬ

በእሷስ አትምጡብኝ እሷ ናት ድርሻዬ

የእምነቴ ካባ መጎናጸፊያዬ።

ስቃይዋን ባየችው በግብፅ በረሃ

አፏ በደረቀው አጥታ ጠብታ ውኃ

ለትውልድ ለመትረፍ በዛ ትህትናዋ

በእሷስ አትምጡብኝ ዕፁብ ነው ዋጋዋ

መለኪያ የለውም ድንግል አደራዋ።

ስወጣ ስገባ በማሰላስላት

በሄድኩበት ሁሉ የኔነሽ በምላት

በእሷስ አትምጡብኝ ድንግል ጠበቃዬ ናት

ፍጥረትን ችላ የሚል ምንም አንጀት የላት።

ድምጿን እያሰማች ሳትጠፋ ከጎኔ

አይዞህ በምትለኝ የሕይወት ብርሃኔ

በእሷስ አትምጡብኝ በዐይን ብሌኔ

ድንግል ማረፊያዬ ከብሬ እኮ ናት ለኔ።

ከኃይለመስቀል ተስፋዬ

ለንደን

ጥር 2008 ዓ/ም